# የአምባሳደር ማይክል ሬይነር የሕይወት ታሪክ

ማይክል ሬይነር፤ እ.አ.አ. በ1988 የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤትን የተቀላቀሉ ሲሆን፤ በአማካሪ ሚኒስትር ማዕረግ ከፍተኛ የውጭ ጉዳይ አገልግሎት አባል ናቸው። እ.አ.አ. ከመስከረም 2016 ጀምሮ በሰው ሀብት ቢሮ፤ የደረጃ ዕድገት እና ምደባ ክፍል ዳይሬክተር በመሆን አገልግለዋል። እ.አ.አ. ከነሐሴ 2015 እስከ ነሐሴ 2016 ድረስ በካቡል (አፍጋኒስታን) የሚሲዮኑ ምክትል አምባሳደር በመሆን የውጭ አገልግሎትን፤ የፀረ- አደንዛዥ ዕፅ እንቅስቃሴን፤ የሕግ ማስከበርን እንዲሁም የሚሲዮኑን ቆንስላ፤ አስተዳደር እና ፀጥታ ዘርፎችን በበላይነት መርተዋል። እ.አ.አ. ከ2012 እስከ 2015 ደግሞ በቤኒን የአሜሪካ አምባሳደር፤ እንዲሁም እ.አ.አ. ከ2010 እስከ 2012 የአፍሪካ ጉዳዮች ቢሮ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና ዋና ዳይሬክተር በመሆን አገልግለዋል። አብዛኛውን የሥራ ጊዜያቸውን በአፍሪካ ያሳለፉ ሲሆን፤ በሐራሬ፤ ዊንድሆክ፤ ኮናክሪ እና ጂቡቲ የአስተዳደር ሹም፤ በብራዛቪል የጠቅላላ አገልግሎት ሹም በመሆን ሰርተዋል። በተጨማሪም፤ በአፍሪካ ጉዳዮች ቢሮ፤ የዚምባብዌ ጉዳይ መኮንን፤ በህግ  ጉዳዮች ቢሮ ልዩ ረዳት እና የህግ አስተዳደር መኮንን፤ እንዲሁም፤ በሉግዘምበርግ የቆንስላ መኮንን ነበሩ። ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ከተበረከቱላቸው ሽልማቶች ውስጥ፤ እ.አ.አ. የ2008 ሊሞን ሀንት ሽልማት ለአስተዳደራዊ ልህቀት፤ በርካታ ከፍተኛ የውጭ አገልግሎት አፈጻጸም ሽልማቶች እና የላቀ የክብር ሽልማቶች ይገኙበታል። አምባሳደር ሬይነር ከላፋየት ኮሌጅ በዓለም አቀፍ ጉዳዮች የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም የማስተርስ ዲግሪያቸውን በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ ከኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል። ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ናቸው።